**አሻጋሪው መሪ !**

አጭበርባሪው አብይ አህመድ አሻግራለሁ ብሎ ከመጣ ጨምሮ እያጭበረበረና እያደናገረ በብዙ አድርባይ ታጅቦ አማራውን፣ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይንና የኦሮሙማን የመስገብገብና የአረመኔነት መንገድ አደገኛነት ተረድተው ይቃወማሉ የሚላቸውን ሁሉ እያስጨፈጨፈ "**ከህይወት ወደ ሞት እያሻገረ**" ነው።

ታቅዶ በሚከናወን በየአንዳንዱ የንፁህን ዘግናኝ ጭፍጨፋ ህይወታቸውን ላጡት ወገኖቻችን መታሰቢያ ይሆን ዘንድ እነሆ የሀዘን እንጉርጉሮ፣

አሻጋሪው መሪ፣ አርቆ አሻገረ
ህይወትን ወደሞት፣ እየመነዘረ።
ስቃይህ ተሰማኝ፣ ወገኔ ጉዳትህ
በአረመኔ እጅ ወድቀህ፣ ትጨፈጨፋለህ!
ሰፋሪ ብሎሀል፣ ወራሪው በእርስትህ።
ጥቃት የማያስቆም፣ ተደማሪ ዜጋ
በደምህ ሲቀልድ፣ ቆሞ እያዘናጋ
አመመኝ ጨነቀኝ፣ እንዴት ልረጋጋ!
ሞትህ ሞቴ ሁኖ፣ ህመምህ ህመሜ
የቀኑ ሳያንሰኝ፣ ትመጣለህ በልሜ።
ለማን አቤት ይባል፣ ማን ይድረስላችሁ?
የሰው ጀግና የለው፣ ቀን ነው የከዳችሁ።
እንባ በማያብስ፣ አቅመቢስነቴ
ገዳይ ካባ አልባሹ፣ ሲገዛህ ማየቴ
የሰቆቃውን ድምፅ፣ ሁሌ መስማቴ
ዘግናኝ አሟሟትህ፣ ተጋርጦ ከፊቴ
መቸም አልረሳችሁ፣ እስከለተ ሞቴ
ሁኖ እየተሰማኝ፣ ልጆቸን ከፊቴ
ቆራርጠው ሲጥሉ፣ አውጥተው ከቤቴ
በእናትነት ሀዘን፣ ተላወሰ አንጀቴ።
አዛውንቱን ሳስብ፣ እንደእኔ እናት አባት
ልጆቹም ልጆች፣ በአጭር የሚቀጩት
በድብርብ ሃዘን፣ ነፍሴን ተበተቧት።
**ከህይወት ወደሞት፣ በተላከ ጥሪ**
**አየነው ሲያሻግር፣ አሻጋሪው መሪ!**

አማራ አስጨፍጭፎ፣  አርቆ ቀባሪ

አብይ ወንጀለኛ፣  አብይ መሰሪ።

የዘር ጭፍጨፋውን፣ በአፉ እያቃለለ

ገሎ ይቀርብሃል፣  ግጭት ነው እያለ።

እናንት የማታዝኑ፣  ሞት የማይነካችሁ

የድሀ ደም እምባ፣  የተጠየፋችሁ

የላይኛው ጌታ፣  ልቦና ይስጣችሁ።

ይብላኝ ለነገ ሟች፣ የዛሬ ተረኛ

በደም የጨቀየ፣ ጨካኝ ወንጀለኛ።

ይብላኝ ሌላው ዜጋ፣ ዛሬን ቆመህ ያየህ

ኦሮሙማ ለአንተም፣ ሞት የደገሰልህ።

ቁመህ የተሳለቅከ፣  በዚህ ሁሉ ሬሳ

በኦሮሙማ እቅድ፣  ነግ በኔን አትርሳ።

እምቢ በል አማራ፣ አቀርባለሁ ጥሪ

ብዙ አትዘናጋ ፣  አትሙት እንደፈሪ

ተስፋ የጣልክበት፣  ብሎሀል ሰፋሪ

ማንም አይደርስልህ፣ ካልመከትክ ወራሪ።

ዘውዲቱ የማነ

2020-11-02